www.ethiopianorthodox.org

# እጠበኝ አምላክ

እጠበኝ አምላክ እነፃለሁ
እጠበኝ ጌታ እነፃለሁ
ኃጢአቴ እንደ አለላ ብትሆንም
ኃጢአቴ እንደ ደም ብትቀላም
እንደ ባዘቶ ትጠራለችና

**አዝማች**

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እጠበኝ አምላክ) | የኔን መተላለፍ | (እጠበኝ ጌታ) | አውቀዋለሁና |
| »» »» | ኃጢአቴም ሁልጊዜ | »» »» | በፊቴ ነውና |

**አዝማች**...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እጠበኝ አምላክ) | የማዳንህን ደስታ | (እጠበኝ ጌታ) | ጌታ ሆይ ስጠኝ |
| »» »» | በእሽታ መንፈስ | »» »» | አምላክ ደግፈኝ |

**አዝማች**...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እጠበኝ አምላክ) | በሂሶጵ ብትረጨኝ | (እጠበኝ ጌታ) | እነፃማለሁ |
| »» »» | ከበረዶም ይልቅ | »» »» | ነጭ እሆናለሁ |

**አዝማች**...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እጠበኝ አምላክ) | ሐሴትና ደስታን | (እጠበኝ ጌታ) | ጌታ ሆይ ስጠኝ |
| »» »» | ምሕረት ይቅርታህ | »» »» | ዘወትር አይራቀኝ |

**አዝማች**...

# <u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u>

ኑኃሚን ደጓ ሴት ዛሬስ ምን ሆንሻል
ደስታ ከአንቺ ርቆ ኃዘን ጸንቶብሻል
በሞዓብ ከአገኘሽ ዘይትና ስንዴ
እባክሽ አንቺ ሴት አትጽናኚም እንዴ
ስደተኛ ነኝ ለአገሩ እንግዳ
ለሞዓብ ሰዎች የሆንኩኝ ባዳ
እንባዬ ይፈሳል በዓይኖቼ ሞልቶ
በሰው ሀገር ላይ ወዳጄን አጥቶ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

አይዞሽ እናታችን እጅግ አትከፊ
ይህን የጭንቁን ቀን በጽናት እለፊ
ድንገት እንደዘበት ታሪክ ይለወጣል
የማይተውሽ ንጉሥ ሊረዳሽ ይመጣል
እባካችሁ ተውኝ ሩትና ዖርፋ
ዕድለ ቢስ ሆንኩ ኑሮዬም ከፋ
ልጆቼም ራቁኝ ሞት ወሰዳቸው
ናፍቀዋልና ወደ አባታቸው
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

ኑኃሚን ኢትዮጵያ ታላቂቷ ምድር
ስለምን ተሞላሽ ሁከትና ሽብር
የመከራ መሬት ሆነሽ አኬልዳማ
እስከ መቼ ድረስ እንደዚህ እማማ
መራራውን ወይን አስጎንጭቶኛል
መንገዴን ሁሉ በእሾህ አጥሮብኛል
ፍቅርና ሰላም ርቋል ከቤቴ
ያስጨንቀኛል ብቸኝነቴ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

በጊዜው ይሆናል እርሱ የፈቀደው
በስሙ ለሚያምኑት ነገር ለበጎ ነው
የአሕዛብን ሰልፍ ከቅጥርሽ ያግዳል
በቦዔዝ አዝመራ ዳዊት ይወለዳል
ያርግልኝ በእውነት ልጽናና በእርሱ
ልቤን ያበርታው ቅዱስ መንፈሱ
በሰላም ይደር ምስኪኑ ወገኔ
የአገሬን ጥፋት አልየው በዓይኔ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል